# የህወሀት/ኢህአዴግ መግለጫ ግልፅ መልእክት ሰጥቷል!!

ከአቶ ለማ ልዩ
(ቱርክ፣ ኢስታንቡል)

በቅድሚያ በወልቃይት የአማራ ህዝብ የድንበር ማካለል ጥያቄ አንስቷል እንዴ? ግራ የገባው ኢህአዴግ ምንድነው የሚለን? ነው፣ ወይስ እንደተለመደው ህዝብን የማዘናጊያ ስልት ነው። እስከማውቀው ድረስ እኛ ወልቃይቴዎች አማራ እንጂ ትግሬዎች አይደለንም የሚል የህዝብ ጥያቄ መኖሩን እንጂ ይሄ ተራራ የትግራይ ያኛው ሸንጥሮ የአማራ ይሁን የሚል የህዝብ ድምፅ በጭራሽ የለም። ደግሞስ በአማራ ህዝብ ጉዳይ ህወሀትና ብአዴን ምንድናቸው? በተጭበረበረ ምርጫቸው እንደህጋዊ የህዝብ ተወካይ አድርገን ብንቆጥራቸው እንኳን የፖለቲካ ፓርቲዎች የህዝቦችን የማንነት መብት የሚወስኑት ምን ስለሆኑ ነው? የሆኖ ሆኖ የሌለ የድንበር ይካለል ጥያቄ ያለ በማስመሰል ጫወታውን በማሾር ህወሀት በሰለጠነችበት የማጭበርበር ስልት መጓዝ ጀመረች ማለት ነው።

ወልቃይት አማራ ነኝ ካለ ምን ትሆኑ? ሌላው የኢህአዴግ ያልበሰለና እርባ ቢስ የተሀድሶ ቃል እየደጋገመ "በተፈጠረው እድገት የህዝብ ፍላጎት በማደጉ" የሚለው ፍሬከርስኪ አባባል ነው። ምንድነው፣ የህዝብ ፍላጎት ማደግ ማለት? የህዝብ ፍላጎት እድገት የሚለካው በምንድነው? በቀን ሶስት እንጀራ ሳይበላ ወደ 6 እንጀራ አደገ ማለት ነው? አንድ የመኖሪያ ቤት ሳይኖረው ትርፍ ቤት አማረው ነው? አንድ ኮት ሳይለብስ ሁለተኛ መደረብ አሰኘው ነው ማለት ነው? የሚነዳው መኪና ሳይኖረው የመኪና ፓርኪንግ ፈለገ ማለት ነው? ኢህአዴግ የህዝቡን የፍላጎት እድገት የሚለካው ምን ሚዛን ነው? ልማት የአምሮትና የምኞት ጉዳይ ሳይሆን የፖሊሲና የአፈፃፀም ስኬት ነው። የህዝብን ተጠቃሚነትና የሀገሪቱን እድገት በማከለ መልኩ ከመስራት ውጪ ህዝብ ያማረውንና የተመኘውን የሚያሟላ ኢህአዴግ የለም። በየትኛውም ሀገር ያለ ህዝብ ማጣት ካልከለከለው በስተቀር ፍላጎት መሰረታዊ አለው። የኢህአዴግ የፍላጎት እድገት የቃላት ጫወታ የመሸንገል የደንቆሮዎች ስልት ካልሆነ በስተቀር ፍላጎትን ለማሟላት ስለሚችሉ አይደለም።

✔✔✔ እኮ ህዝብ በናንተ ሚዛን ምንድነው ያማረው? በህዝቦች አይን ከዚህ በታች ያለው ተጨባጭ እውነታ በደንብ አምሮታል። ከቻላችሁ ተግብሩት ካልቻላችሁ ስልጣን ርስት ስላይደለ ቦታውን ልቀቁት። እነቡልቻ ደመቅሳን የመሳሰሉ ምሁራን ከጫካ እውራን በተሻለ መስራት እንደሚችሉ እርግጠኞች ነን።

✔✔✔ እኔ ልንገራችሁ፣ እናንተ የምትሉትን አይነት የእርጉዝ ሴት አምሮት የለውም። የኢትዮጵያ ህዝብ ያማረው ዲሞክራሲያዊ መንግስት ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ያማረው ተጠያቂነት ያለበትና የህግ የበላይነት የሰፈነበት ስርአትን ማየት ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ያማረው ህግ ብቻ የሚተገበርበትና ከካድሬ የፀዳ ነፃ ፍርድ ቤቶችን ማግኘት ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ያማረው በህዝብ እምነት የተጣለበት፣ ታዛቢዎች ያደነቁለት ተአማኒ ምርጫ በዚህች ሀገር በፀሀይ ብርሃን ማየት ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ያማረው ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ፣ የመሰብሰብ፣ የመሰለፍ መብቶች የተረጋገጠባትና ያለመሸማቀቅ፣ ያለፍርሃት የፈለገውን ፓርቲ የመደገፍ መብት የተከበረበትን ስርአትን ማየት ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ያማረው የአፈና፣ የዘረፋ፣ በዘርና በቡድን ተደራጅተው ትናንሽ መንግስት የተፈጠሩበት፣ አይነኬ የሆኑበት ስርአት ፈርሶ ማየት ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ያማረው በስልጣን የባለጉ፣ የህዝብ ገንዘብ የዘረፉ፣ የገረፉ፣ የገደሉ በህግ ተጠያቂ ሲሆኑ ማየት ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ ያማረው ህዝብ ሲፈልግ የሚሾመው፣ እምነት ካጣበት የሚሽረውን ዘመን ማግኘት ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ያማረው ህወሀት የምታሽከረክረው የጀነራሎች መንግስት ሳይሆን ሰራዊትና ሲቪል አስተዳደር ያልተቀላቀለበትን ስርአት ማየት ነው። ፓርቲና መንግስት፣ ወታደርና ህወሀት በየስፍራቸው ተለይተው ማየት ይሻል። ይህን

መሻት ኢህአዴህ እንደቀላል ጉዳይ አልፎታል። ምንም እንዳልተፈጠረ ንቆ ትቶታል።

ጠመንጃዬ በእጄ ብሏል። ይህን አይነቱን የህዝብ ስርአት ለማቆምና ከዚህ አይነት አደጋ ነፃ ለመሆን በቅድሚያ የሚወስዳቸውን እርምጃዎች ኢህአዴግ ሳይገልፅ በሽፍንፍን የዲስኩር ንባብ ማጠቃለሉ የሚያሳየን ነጥብ ይህቺን ሀገር ከጥፋት ለማዳን ፍላጎቱም፣ አቅሙም እንደሌለው ብቻ ሳይሆን ተመሳሳይ ጥያቄና የህዝብ ጩኸት ላለመስማት በታንክ ጥይት የህዝብን ተቃውሞ ለመጨፍለቅ የዘመቻ ዝግጅቱን መጨረሱን ነው። እንዲህ ደረቱን ነፍቶ የበሰበሰ የስርአቱን ቆሻሻ መልክ በድሪቶ ፅሁፍ ለመሸፈን የፈለገው የሀይል ዝግጅቱን ማጠናቀቁንና ያፈተለከ ጋኔን የሚለውን ህዝብ ባዘጋጀለት የአፈና ጠርሙስ ውስጥ ጨፍልቆ ለመክተት ማቀዱን ነው። የአማራና የኦሮሞ ህዝብ ሆይ፣ ኢህአዴግ ለጥያቄዎችህ መልስ የለውም። ያወጣልህን የንባብ ሀተታ ሰምተህ ወደቤትህ ካልገባህ የሀተታው ትርጓሜ የሚያስረዳው ሰጥ፣ ለጥ አድርጌ በሀይል እጨፈልቃለሁ ማለቱ ነው።

✔✔✔

አጠቃላይ የስርአቱ ኢ-ህገመንግስታዊ ተግባርና ተግባሩ ያስከተለውን ውጤት ለመቀበል አልፈለገም። እንደተለመደው በመልካም አስተዳደር ረገድ የታየውን ጉድለት ለመሙላት ቀልቤሳን በሓጎስ፣ መሀመድን በግጨው እቀይርልሃለሁ፣ ፍላጎትህ ስላደገ ደግሞ ስኳርና ጨው አቀርብልሃለሁ በሚል ማላገጥ የቆሰልክለትን፣ የሞትክለትን አላማ በሹፈት አልፏል። ስራ ያጣህ ምድረ ተማሪ ሁላ ከጎዳና ላይ ጩኸት ወደማዘጋጅልህ የኮብል ስቶን ስራ ሰተት ብለህ ግባ እያለ ነው። ወጣት ህገመንግስታዊ መብትን መጠየቅና ይከበርልኝ ማለት የሚያስችል ብቃትም፣ እውቀትም የለህም እያለ ነው። መብት ብንስጥህ ታበላሸዋለህ፣ የሻእቢያና የግንቦት ሰባት ተላላኪ ሆነህ ትቀራለህ እያለ ነው። ህገ መንግስትም፣ መንግስትም፣ ፓርቲም እኔ ስለሆንኩ እኔ በተሻለ ላንተ አውቅልሃለሁ እያለ ነው።

ከእንግዲህ ያለ ምርጫ ምንድነው?

✔✔✔ ባርነት ውስጤ ነው ወይም ነፃነቴ በእጄ ነው የሚለው አንኳር ነጥብ የወቅቱ ጥያቄ በግልፅ ሆኗል። ከዚህ ውጪ ከኢህአዴግ የተሰጠ የህዝብ ጥያቄ ምላሽም የተደረገ የስርአት ተሃድሶ የሚባል ነገር የለም።